# ዚማ ለመካድና ኃይሉን ለመስበር የሚደረግ ጸሎትና እወጃ

## *የኑዛዜ ጸሎት*

*አፍቃሪ እግዚአብሔር ሆይ ኃጢአትን በመስራት ካንተ ዘወር ማለቴን እናዘዛለሁ። ሌሎች ሰዎችን ያስፈራራሁበትን እና በሰዎች ላይ የበታችነትን እንዲሁም ውርደትን የጫንኩበትን በደሌን ይቅር በለኝ። ስለ ትዕቢቴ ይቅር በለኝ። ሌሎችን የጎዳሁበትን እና የጨቆንኩበትን በደሌን ይቅር በለኝ። እነዚህን ሁሉ ነገሮች በኢየሱስ ስም ክጃያቸዋለሁ።*

*የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ሆይ በከርስቶስ በመስቀል ላይ ስለተገኘው የይቅርታ ስጦታ አመሰግንሃለሁ። አንተ እንደተቀበልከኝ ዕውቅና እሰጣለሁ። በመስቀል በኩል ካንተ ጋር እና ከሌሎች ጋር መታረቅ ስለሆነልን አመሰግንሃለሁ። ልጅህ መሆኔን እና የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽ መሆኔን ዛሬ አውጃለሁ።*

## *እወጃዎችና ክህደቶች*

*አባት ሆይ የፍርሃት ተገዢ አለመሆኔን ነገር ግን የፍቅርህ ልጅ መሆኔን ካንተ ጋር እስማማለሁ። ሙሐመድ ያስተማረውን የእስልምና ፍላጎቶች ሁሉ እቃወማለሁ እክዳለሁ። በማንኛውም መንገድ ለቁርአኑ አላህ የሚሆነውን መገዛትን እክዳለሁ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ የሆነውን እርሱን ብቻ እንደማመልክ አውጃለሁ።*

*ለዚማ ውል እና መርሆች ለመገዛት በመስማማት አባቶቻችን ለሰሩት ኃጢአት ንስሃ እንገባለን የኃጢአታቸውንም ይቅርታ እንጠይቅሃለን።*

*ለእስልምና ማህበረሰብ እና መርሆች ለመገዛት በኔም ሆነ በዘሮቼ የተደረጉትን ውሎች ሁሉ እክዳለሁ።*

*ዚማንና አኳሆኖቹን ሁሉ ሙሉ በሙሉ እቃወማለሁ። በጂዝያ ክፍያ ጊዜ አንገት ላይ የሚደረገውን ምልክት ከነትርጉሙ እክዳለሁ። በተለይ በዚህ ስርአት የተመሰለውን የእርድ እና የሞት እርግማን እክዳለሁ።*

*የዚማ ውል በክርስቶስ መስቀል ላይ መቸንከሩን አውጃለሁ። ዚማ በአደባባይ ስለተዋረደ በኔ ላይ ስልጣን የለውም። የዚማ ውል መንፈሳዊ መርሆች በክርስቶስ መስቀል መጋለጡን፣ እርቃኑን መቅረቱን እና መዋረዱን አውጃለሁ።*

*ለእስልምና ያለኝን የውሸት ክብር ስሜት እክዳለሁ።*

*የውሸት የህሊና ክስን እክዳለሁ።*

*ማታለልን እና ውሸትን እተዋለሁ።*

*በክርስቶስ ያለኝን እምነት ላለመናገር የገባሁትን ውል ሁሉ እክዳለሁ።*

*ስለ ዚማ ወይንም ኢስላም ላለመናገር የገባሁትን ውል ሁሉ እክዳለሁ።*

*እናገራለሁ ዝምም አልልም።*

*እውነት አርነት እንደሚያወጣኝ አውጃለሁ።[1] በክርስቶስ ኢየሱስ ነፃ እንደወጣ ሰው መኖር ምርጫዬ ነው።*

*በኢስላም ስም በኔና በቤተሰቦቼ ላይ የተነገሩትን እርግማኖች ሁሉ እክዳለሁ አመክናለሁ። በዘሮቼ ላይ የተነገሩትን እርግማኖች ሁሉ እክዳለሁ አመክናለሁ።*

*በተለይ የሞትን እርግማን እሰብራለሁ። ሞት ሆይ በኔ ላይ ስልጣን የለህም!*

*እነዚህ እርማኖች በኔ ላይ ስልጣን እንደሌላቸው አውጃለሁ።*

*የክርስቶስን በረከቶች እንደመንፈሳዊ ውርሶቼ አድርጌ አውጃለሁ።*

*ፍርሃትን እክዳለሁ። በክርስቶስ ደፋር መሆን ምርጫዬ ነው።*

*የሰዎች መጠቀሚያ መሆንንና በቁጥጥራቸው ስር መሆንን እክዳለሁ።*

*ጭቆናና የኃይል ጥቃትን እክዳለሁ።*

*ፍርሃትን እክዳለሁ። በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የማጣት ፍርሃትን እክዳለሁ። የድህነትን ፍርሃት እክዳለሁ። ባርያ የመሆን ፍርሃትን እክዳለሁ። ተገዶ የመደፈርን ፍርሃት እክዳለሁ። ብቸኛ የመሆንን ፍርሃት እክዳለሁ። ቤተሰቦቼን የማጣት ፍርሃትን እክዳለሁ። የመገደልን እና የሞትን ፍርሃት እክዳለሁ።*

*እስልምናን መፍራትን እክዳለሁ። ሙስሊሞችን መፍራትን እክዳለሁ።*

*በሕዝባዊ ወይንም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ ፍርሃትን እክዳለሁ።*

*ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉ ጌታ መሆኑን አውጃለሁ።*

*ኢየሱስን በሁሉም የህይወቴ ክፍሎች ላይ ጌታ አድርጌ ራሴን እሰጠዋለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ የቤቴ ጌታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሃገሬ ጌታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ሃገር ውስጥ ባሉ ሰዎች ሁሉ ላይ ጌታ ነው። ኢየሱስን እንደ ጌታዬ አድርጌ ራሴን እሰጠዋለሁ።*

*ውርደትን እክዳለሁ። ክርስቶስ እንደተቀበለኝ አውጃለሁ። እርሱንና እርሱን ብቻ አገለግላለሁ።*

*እፍረትን እክዳለሁ። በመስቀሉ በኩል ከሁሉም ኃጢኣት መንጻቴን አውጃለሁ። እፍረት በኔ ላይ መብት የለውም። ከክርስቶስ ጋር በክብር እነግሳለሁ።*

*ጌታ ሆይ ሙስሊሞችን ስለመጥላታችን እኔንና ዘሮቼን ሁሉ ይቅር በለን። ሙስሊሞችንና ሌሎችን መጥላትን እክዳለሁ። የክርስቶስን ፍቅር በዚህ ምድር ላይ ላሉ ሰዎች ሁሉ አውጃለሁ።*

---

1. *ዮሃ 8:32*

ስለቤተ ክርስቲያን ኃጢኣትና መሪዎች በተሳሳተ መንገድ ስለመገዛታቸው ንስሃ እገባለሁ።

ማግለልን እክዳለሁ። በክርስቶስ በኩል ይቅርታን ማግኘቴን እና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቴን አውጃለሁ። ከእግዚአብሔር ጋር ታርቄአለሁ። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በሰማይም ሆነ በምድር ውስጥ ያለ ኃይል ለውጥ ሊያደርግብኝ አይችልም።

ምስጋናዬን ወደ አባታችን እግዚአብሔር፣ ብቸኛ አዳኜ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ፣ ብቻውን ህይወትን ወደሚሰጠኝ ወደ መንፈስ ቅዱስ ከፍ አድርጌ አነሳለሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ መሆኑን ህያው ምስክር ለመሆን ራሴን አሳልፌ እሰጠዋለሁ። በመስቀሉ አላፍርም። በትንሳኤው አላፍርም።

የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብ አምላክ በሆነው የህያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኔን አውጃለሁ።

የእግዚአብሔርንና የመሲሁን ድል አውጃለሁ። ጉልበት ሁሉ እንደሚንበረከክ እና ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚመሰከር አውጃለሁ።

በዚሚ ስርኣት ውስጥ በመሳተፋቸው ለሙስሊሞች ይቅርታን አውጃለሁ።

አባቴ እግዚአብሔር ሆይ እባክህን ከዚማ፤ ከዚሚ መንፈስ እና እግዚአብሔራዊ ካልሆነ ከዚማ ጋር ከተያያዘ መርህ ሁሉ ነፃ አውጣኝ።

አሁን በቅዱስ መንፈስህ እንድትሞላኝ እና የኢየሱስ ክርስቶስን መንግስት በረከቶች ሁሉ በኔ ላይ ታፈስ ዘንድ እጠይቅሃለሁ። የቃልህን እውነት አጥርቼ መረዳት እችል ዘንድ እና በእያንዳንዱ የህይወቴ ገጽታ ላይ ተግባራዊ ማድረግ እችል ዘንድ ጸጋህን ስጠኝ። የህይወትንና የተስፋን ቃሎች አደርጋለሁ ብለህ ቃል በገባኸው መሰረት ትሰጠኝ ዘንድ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በስልጣንና በኃይል መናገር እችል ዘንድ ከናፍርቴን ትባርክ ዘንድ እለምንሃለሁ። ለክርስቶስ ታማኝ ምስክር እሆን ዘንድ ድፍረትን ስጠኝ። ለሙስሊሞች ጥልቅ ፍቅርንና የክርስቶስን ፍቅር ከነርሱ ጋር መካፈል እችል ዘንድ ሸክምን እንድትሰጠኝ እለምንሃለሁ።

እነዚህን ነገሮች አዳኝና ጌታ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አውጃለሁ እጠይቃለሁ።

አሜን።